የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 65
ADDIS ABABA, 2nd September, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፮/፪ሺ፲፯

የስታርታፕ አዋጅ …...................ገጽ ፲፱ሺ፩፻፹፩

**Content**

Proclamation No. 1396/2025

Startup Proclamation …………......Page 19181

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፮/፪ሺ፲፯

## የኢትዮጵያ ስታርታፕ አዋጅ

በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የስታርታፕ ውጤት በሒደት ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችንና ኩባንያዎችን በማፍራት ለኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ጉልህ ሚና እያበረከተ በመሆኑ፤

ስታርታፕ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ አቅም በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን ለማፋጠን ቁልፍ ሚና ያለውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችል በመሆኑ፤

ምቹ የስታርታፕ ምህዳርን በመገንባት ስታርታፖችን ውጤታማና ስኬታማ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ስታርታፖች እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎችን ዒላማ ያደረገ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል የተሳለጠ የስያሜ፣ የዕውቅና እና የአቅም ግንባታ አተገባበር ሥርዓት በመዘርጋት ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ እመርታን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1396/2025

## ETHIOPIAN STARTUP PROCLAMATION

**WHEREAS,** globally the results of startups supported by innovation and technology are gradually contributing to economic growth and development by creating large industries and companies;

**WHEREAS,** Since startups play a key role in accelerating economic growth and development by harnessing Ethiopia's potential and enabling it to become globally competitive;

**WHEREAS,** since it is important to make startups effective and successful by building a conducive startup ecosystem;

**WHEREAS,** it is important to ensure sustainable technological and economic progress by establishing a streamlined system of designation, accreditation, and capacity building that provides targeted, integrated support to startups and startup ecosystem builders;

ስታርታፖችን እና የስፓርታፕ ምህዳር ገንቢዎችን የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ አቅርቦት ተግዳሮቶች እና የፋይናንስ ስጋትን በዘላቂነት ለመቅረፍ የግራንት ፕሮግራም፣ የብድር ዋስትና ማዕቀፍ እና የፈንዶች ፈንድ መዋቅርን ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ዓዋጅ "የስታርታፕ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፮/፳፻፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ስታርታፕ"** ማለት ምንም የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ታሪክ ሳይኖረው ወይም የተወሰነ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ታሪክ ብቻ ኖሮት፤ ኢኖቬሽንን ተግባራዊ የሚያደርግ፣ የቴክኖሎጂ ወይም በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ተመንዳጊ እና የገበያ መዋቅር የሚለውጥ ምርትን፣ አገልግሎትን ወይም ሒደትን በማስተዋወቅ፣ በመፍጠር፣ በማበልፀግ፣ ሽግግርና ማላመድ በማድረግ፣ ወይም በምልስ-ምሕንድስና አማካኝነት ኢኮኖሚያዊ ዕሴትን በመፍጠር ላይ የተሰማራ ቡድን ወይም ሰው ነው፤

፪/ "**አክሰለሬተር**" ማለት ጥልቀት ያለው፣ በጊዜ የተገደበና የስታርታፕ ምሥረታ፣ ዕድገት እና ልማት ለማገዝ የተቀረጸ፤ በተቋም የሚከናወን ፕሮግራም ወይም ይህንን የሚያከናውን ሰው ነው፤

**WHEREAS,** it is necessary to organize a grant program, credit guarantee framework, and fund of funds structure to sustainably address the financing challenges and financial risks faced by startups and startup ecosystem builders;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Startup Proclamation No. 1396/2025".

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Startup"** means a person or a group, with no or limited business history who is engaged in creating economic value through the introduction, creation, transplantation, or reverse engineering of a product, service, or process that implements innovation, technology, or technology enabled scalable, and market-changing;

2/ **"Accelerator"** means a person, or a program hosted by an entity that provides an intensive, time-bound program designed to support the establishment, growth, and development of Startups;

፫/ **"ምክር ቤት"** ማለት በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፭/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ስድስት ፮ መሠረት የተቋቋመው የብሔራዊ ዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት ነው፤

፬/ **"ኢኮኖሚያዊ ዕሴት"** ማለት በኢኮኖሚው ዕድገት ላይ በተጨባጭ የሚታይ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፭) ከተጠቀሱት የኢኮኖሚ አመላካቾች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት ሊለካ የሚችል አዎንታዊ ተጽዕኖ ነው፤

፭/ **"የኢኮኖሚ አመላካቾች"** ማለት የስታርታፕ ኢኮኖሚያዊ ዕሴት ለመለካት የሚያስችሉ አመላካቾች ሆነው የቅልጥፍናና ምርታማነት ጭማሪን፣ የስራ ዕድል ፈጠራን፣ የውጭ ንግድ ዕድገትና ብዝኀ-ዘርፍነትን፣ ኢኖቬሽንንና የማህበራዊ ደህንነት ማሻሻልን ያጠቃልላል፤

፮/ **"የውጭ ባለሀብት"** ማለት የውጪ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሥራ ላይ ያዋለ፡-

ሀ) የውጭ ሀገር ዜጋ፤

ለ) የውጭ ሀገር ዜጋ በባለቤትነት የተሳተፈበት ድርጅት፤

ሐ) በማንኛውም ባለሀብት ውጭ ሀገር የተቋቋመ ድርጅት፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፮) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) በተመለከቱት ማናቸውም ባለሀብቶች መካከል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት ፤ ወይም

ሠ) እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ውጭ ሀገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

3/ **"Council"** means the national digital economy council established by electronic transaction Proclamation No. 1205/2020 Article 6;

4/ **"Economic Value"** means a demonstrably positive impact on the growth of the economy, measurable through one or a combination of economic factors provided under Sub-Article (5) of this Article;

5/ **"Economic Factors"** means factors that helps to measure the economic value of Startups and includes increased efficiency and productivity, job creation, export growth and diversification, innovation, and social welfare enhancement;

6/ **"Foreign Investor"** means any one of the following who has invested foreign capital in Ethiopia:

a) A Foreign national;

b) An enterprise in which a foreign national has an ownership stake;

c) An enterprise incorporated outside of Ethiopia by any investor;

d) An enterprise established jointly by any of the investors specified under Sub-Article (6) paragraph (a), (b) or (c) of this article; or

e) An Ethiopian permanently residing abroad and preferring treatment as a foreign investor.

፯/ **"የውጭ ስታርታፕ"** ማለት በዚህ አዋጅ የስታርታፕ ስያሜ ያገኘና ሙሉ በሙሉ በውጭ አገር ዜጋ ወይም በውጭ አገር ዜጋ ከካፒታል ድርሻው ከግማሽ በላይ ድርሻ ከኢትዮጵያዊ ጋር በጋራ ባለቤትነት የተያዘ ስታርታፕ ነው፤

፰/ **"ኢንኩቤተር"** ማለት የስታርታፕ ዕድገትና ልማት ለማፋጠን አመቺ የሆነ ከባቢን እና ሀብቶችን ለስታርታፕ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

፱/ **"ኤንጅል ኢንቬስተር"** ማለት የራሱን መዋዕለ ነዋይ በስታርታፖች ላይ በማፍሰስ ጥቅም ላይ ያዋለ ሰው ነው፤

፲/ **"ግራንት"** ማለት በመጀመሪያ የእድገት ደረጃዎች ላይ ያሉ ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ ወደ ስራ ማስገቢያ ልማትና የንግድ ስራ ሂደት ጋር የሚያያዙ ወጪዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚቀርብ ገንዘብ ነው፤

፲፩/ **"ቬንቸር ካፒታል"** ማለት በገንዘብ በቴክኒክ ወይም በአስተዳደር እውቀት የእድገት አቅም ላላቸው ስታርታፖች ኢንቨስት የሚያደርግ ሰው ነው፤

፲፪/ **"ኢኖቬሽን"** ማለት የአዲስ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሒደት ፈጠራ፣ ልማትና ትግበራ ወይም አዳዲስ መፍትሔዎችን ወይም በሥራ ላይ ባሉት መፍትሔዎች ላይ የተደረገን ጉልህ ማሻሻያ የሚወክል ድርጊት ነው፤

፲፫/ **"ባለሀብት"** ማለት ካፒታሉን ስያሜ ባገኘ ስታርታፕ ወይም ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ያዋለ ሰው ነው፤

7/ **"Foreign Startup"** means a Startup that is designated as a startup under this Proclamation and which is fully owned by a foreign national or jointly owned more than half of its capital between foreigner and Ethiopian national;

8/ **"Incubator"** means a person that provides a supportive environment and resources for Startups to foster their growth and development;

9/ **"Angel Investor"** means a person who invests his own capital in startups;

10/ **"Grant"** means capital provided to a designated startup in the early stages of development to cover costs associated with the development and business process of the startup;

11/ **"Venture Capital"** means a person who invests in startups with financial, technical, or managerial expertise that have the potential to grow;

12/ **"Innovation"** means the creation, development, and implementation of a new product, service or process; or an action that represents new solutions or a significant improvement over existing solutions;

13/ **"Investor"** means a person who invests capital whether in cash or in kind in a Designated Startup or a Designated Startup Ecosystem Builder;

፲፬/ **“ሚኒስቴር”** ወይም **“ሚኒስትር”** ማለት የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፭/ **“የሕዝብ ኩባንያ”** ማለት ሰነዶቹ በሰነደ-መዋዕለ ንዋይ ገበያ ቢመዘገቡም ባይመዘገቡም አክሲዮኖቹ በሰነደ መዋዕለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚሸጡ የአክሲዮን ኩባንያ ነው፤

፲፮/ “**የሙከራ ፈቃድና ክትትል**” ማለት በስታርታፕለገበያ የሚቀርቡ አዳዲስ ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ሒደቶችን ወደ ገበያ እንዲቀርቡ ይሁንታ ከማግኘታቸው በፊት በተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቁጥጥር እና ክትትል ስር ሆነው በሙከራ ሒደት ውስጥ እንዲያልፉ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ነው፤

፲፯/ **“ተመንዳጊነት“** ማለት ስታርታፕ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የሒደቱ ጥራት፣ ቅልጥፍናና አፈጻጸምን የገበያ ፍላጎት ጫናን በመቋቋም በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ የገበያ ድርሻን ለማሳደግ ያለው አቅም ነው፤

፲፰/ **“የስታርታፕ ስያሜ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰጥ የስታርታፕ ዕውቅና ነው፤

፲፱/ **“የስታርታፕ ምኅዳር”** ማለት ለስታርታፕ መፈጠር፣ ልማትና ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን፣ ዕውቀትንና ድጋፍን የሚሰጡ ተዋንያንና ድርጅቶች ትስስር ነው፤

14/ **“Ministry” or “Minister”** means the Ministry or Minister of Innovation and Technology;

15/ **“Public Company”** means a share company, whether listed on a securities exchange or not, whose shares of stock are traded on a securities exchange or over-the-counter markets;

16/ **“Regulatory Sandbox”** means a regulatory framework that allows for a testing process of new products, services, or processes of Startups under the regulatory authority’s control and oversight, prior to their introduction to the Market;

17/ **“Scalability”** means the ability of a startup to increase its market share at low cost by adapting the quality, efficiency, and performance of its product, service, or process to withstand market demand;

18/ **“Startup Designation”** means the startup designated by the ministry in accordance with this proclamation;

19/ **“Startup Ecosystem”** means the interconnected network of actors and organizations that provide resources, knowledge, and support necessary to foster the creation, development, and growth of Startups;

፳/ **“የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ”** ማለት ኢንኩቤተርን፣ አክስለሬተርን፣ የጋራ ሥራ ቦታን፣ የግል ባለሀብት ፈንድን፣ ቬንቸር ካፒታልን፣ ኤንጅል ባለሀብትን፣ የፋይናንስና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን፣ የምርምርና ማበልጸግ ኤጀንሲዎችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ ለስታርታፕ ምሥረታ፣ ልማትና ዘላቂነት በንቃት አስተዋጽዖ የሚያደርግ ሰው ነው፤

፳፩/ **“በቴክኖሎጂ የታገዘ”** ማለት የተሻሻለ ቅልጥፍናን ፤ ውጤትን እና ኢኖቬሽንን የሚያስከትሉ ሒደቶችን፣ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም የቢዝነስ ሞዴሎችን ለመፍጠር፣ ለማሳደግ፣ ለማመቻቸት ወይም ለመለወጥ፤ አስቻይ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ ማምጣት፣ ትራንስፕላንት ማድረግ ወይም ማዋሐድ ነው፤

፳፪/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተቋቋሙትንና በአንቀጽ ፵፯ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት አዲስ የተደራጁትን ክልሎች፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን የሚያጠቃልል ነው፤

፳፫/ **“የስታርታፕ የፈንዶች ፈንድ”** ማለት በሌሎች የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ በግለሰብ፣ በተቋም ወይም በመንግሥት በጋራ ወይም በተናጠል ሰነደ መዋዕሎችን በባለቤትነት ድርሻ በመያዝ ፈንዱን ስያሜ ባገኘ በሌሎች ፈንድ አድራጊዎች በኩል በስታርታፖች ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ የኢንቨስትመንት ፈንድ ነው፤

20/ **“Startup Ecosystem Builder”** means a person that actively contributes to the establishment, development, and sustainability of Startups and it includes Incubators, Accelerators, Co-Working Spaces, Private Equity Funds, Venture Capitals, Angel Investors, Financial and higher education institutions, technical and vocational education and training institutions, research and development agencies, non-governmental organizations;

21/ **“Tech-Enabled”** means the utilization, adoption, transplantation, or integration of technology to innovate, enhance, optimize, or transform processes, products, services, or business models, leading to improved efficiency, outcomes, and innovation;

22/ **“Region”** means the regions established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and newly organized in accordance with Article 47, Sub-Article (3) Letter (e), and the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

23/ **“Startup fund of funds”** means an investment fund that invests in startups through other fund managers, which are named after the fund, by holding shares in other investment funds, either jointly or separately, with individuals, institutions or governments;

፳፬/ **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፭/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራልና በክልል ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ሥልጣንና ተግባር</u>**

**፬. <u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የስታርታፕ ምህዳር ልማት ተዋናዮች ለስታርታፕ ምቹ ከባቢ እንዲፈጠርላቸው ያስተባብራል፤

ለ) በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የስታርታፕ እና የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢን በኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ስያሜ ይሰጣል፤ ስያሜ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤

ሐ) የስታርታፕ ግራንት ፕሮግራሙን ያስተዳድራል፤

መ) በዚህ አዋጅ መሰረት የተቀመጡ ማትጊያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ስያሜ የተሰጣቸውን ስታርታፕ፣ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢን አፈጻጸም እና አጠቃላይ የስታርታፕ ምህዳር ሁኔታን በየአመቱ ይገመግማል፤ ስለ አፈጻጸማቸውም ሪፖርት ያወጣል።

፪/ ዲጂታል የስታርታፕ ፕላትፎርም ይፈጥራል፤ ያስተዳድራል።

24/ **"Person"** means a physical or juridical person;

25/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall apply at the federal and regional levels.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>POWERS AND FUNCTIONS</u>**

**4. <u>Powers and Functions of the Ministry</u>**

1/ The ministry shall have the following powers and functions to implement the provisions of this proclamation:

a) Coordinates startup ecosystem development actors to create a conducive environment for startups;

b) In accordance with this Proclamation and any rules and regulations issued pursuant to this Proclamation, it shall, at the discretion of the committee, grant a designation to a startup and startup ecosystem developer, renew, suspend or revoke the designation;

c) Manage the Startup Grant Program;

d) Conduct an annual evaluation and issue a report on the performance of Designated Startups and Designated Startup Ecosystem Builders that are recipients of incentives through the mechanisms of this Proclamation.

2/ Create and administer a Digital Startup platform.

፫/ ዲጂታል የስታርታፕ ፕላትፎርም፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ስታርታፕ ምኅዳር አግባብነት ያለው መረጃ የሚገኝበት የአንድ መስኮት አገልግሎት ይሰጣል፤

ለ) የስታርታፕነት እና የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢነት ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ማስተናገጃ ሆኖ ያገለግላል፤

ሐ) በስታርታፕ ምኅዳር ገንቢና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት መካከል ለሚደረጉ መስተጋብር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ ዲጂታል ስታርታፕ ቋቱን በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ለማሳካት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

፭/ የአቅም ግንባታን በሚመለከት የማስተባበርና የመከታተል ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር ሥራዎችን ይፈጽማል፤

፮/ ስታርታፕ እና ኢኖቬሽን በኢኮኖሚው ላይ ስለሚኖራቸው አስተዋጽዖ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠሪያ ሁነቶችን ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል፤ ያስተባብራል፤

፯/ ሚኒስቴሩ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፤ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሌሎች መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፤ እንዲሁም ከግል ዘርፍ ተዋንያን ጋር በመተባበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የችግር ፈቺነት ውድድርና ሽልማት ያዘጋጃል፡፡

3/ The Digital Startup Portal shall:

a) Serve as the single-window access to relevant information about the Startup Ecosystem in Ethiopia;

b) Receive and process applications for Startup Designation and Startup Ecosystem Builder Designation;

c) Serve as a platform for interaction between the Startup Ecosystem Builders and other relevant institutions;

4/ Notwithstanding Sub-Article (3) of this Article, the Ministry may use the Digital Startup Portal to discharge other objectives as may be relevant to the conduct of powers and functions given to it under this Proclamation.

5/ It will work with the ministry of labor and skills, while maintaining its responsibility for coordinating and monitoring capacity building;

6/ Organize and coordinate events to create better understanding of the contribution of startup and innovation to the economy, in collaboration with the ministry of labor and skill;

7/ The ministry, in collaboration with the ministry of labor and skills, the ministry of industry and other governmental and non-governmental institutions, as well as private sector actors, shall organize a problem-solving competition and award at least once a year.

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፯) መሠረት የሚደረገውን ውድድና ሽልማት ዝርዝር ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፭. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

ሀ) ለስታርታፕ እድገት ድጋፍ የሚያደርጉ የመንግስት ተቋማትን፣ የግል ዘርፉን፣ እና የልማት አጋሮች ቅንጅትን በበላይነት ይመራል፤

ለ) ስታርታፖችና የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ የሚቀርቡ ማትጊያዎች ክትትልና ግምገማ ሪፖርቶችን ይገመግማል፤ ያጸድቃል፤

ሐ) ምቹ የስታርታፕ ምኅዳርን ለመፍጠር የሚያስፈልጉ ሀብቶችን ለማመቻቸት የሚረዳ ስትራቴጂ ያጸድቃል ትግበራውንም ይከታተላል፤

መ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የስታርታፕ ግራንት ክፍፍል ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሠ) በገንዘብ ሚኒስቴር የሚዘጋጀውን የስታርታፕ ግራንት መመሪያ ያጸድቃል፤ ተፈጻሚነቱን በበላይነት ይከታተላል፤

ረ) ስያሜ በተሰጣቸው ስታርታፕና የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ላይ የስታርታፕ ግራንት እና እንደ አግባብነቱ የሌሎች ማትጊያዎች ሒሳቦች ላይ ዓመታዊ ኦዲት ከኢትዮጵያ ሒሳብ ሥራና ኦዲት ቦርድ ፈቃድ በተሰጠው የውጪ ኦዲተር እንዲሠራ ያደርጋል፤

8/ The details of the competition and awards to be held pursuant to Sub-Article (7) of this Article shall be determined by a Directive issued by the ministry.

## 5. Power and Function of the Council

1/ The Council shall have the following powers and functions to:

a) Leads the coordination of government institutions, the private sector, and development partners that support startup growth;

b) Review and approve monitoring and evaluation reports on incentives provided to Designated Startups and Designated Startup Ecosystem Builders;

c) Approve a strategy and monitor its implementation to facilitate resources which are needed to create a vibrant Startup Ecosystem;

d) Ensure transparency and accountability in the disbursement of the Startup Grant provided under this Proclamation;

e) Endorse the startup grant Directive to be developed by the Ministry of Finance and ensure its implementation;

f) Initiate annual audits by an external auditor licensed by the Accounting and Audit Board of Ethiopia on the accounts of the Startup Grant and, as relevant, incentives provided to Designated Startups and Designated Startup Ecosystem Builders;

ሰ) አንድ የሒሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በሦስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አጠቃላይ የስታርታፑን እንቅስቃሴ የኦዲት ሪፖርትን ይቀበላል፣ የኦዲት ውጤቶችን ይገመግማል፣ በሪፖርቱ ውስጥ በቀረቡት ምክረ-ሀሳቦች መሠረት አስፈላጊ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ረ) እንደተጠበቀ ሆኖ ዓመታዊው የኦዲት ሪፖርት ተጠቃሎ እንዲታተምና ለሕዝብ መድረሱን ያረጋግጣል፤

ቀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ለስታርታፕ ምኅዳር ልማት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለመለየት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ከመንግስትና ከግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች የተውጣጣ የባለ ድርሻ አካላት ምክክር ያካሂዳል፤

በ) በሚኒስቴሩ የሚቀርቡ የብሄራዊ ስያሜ ኮሚቴ አባላትን እና አሰራሩን በተመለከተ መመሪያ ያጸድቃል፤

ተ) በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ኀላፊነቶቹን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል።

፪/ ምክር ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባር በሕግ ለሚቋቋመው የሀገራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ያስተላልፋል።

g) No later than Three months after the end of the fiscal year, receive audited report and review audit results and ensure that the necessary actions are taken according to the recommendations thereof;

h) Notwithstanding to the provisions of Subparagraph (h) of this Sub Article, ensure that the annual audit report is compiled, published and made available to the public;

i) Hold a stakeholders consultation composed of public and private sector participants at least once a year to identify obstacles that hamper the development of the Startup Ecosystem in Ethiopia;

j) Approves Directives regarding the members of the national designation committee and its procedures, as proposed by the ministry;

k) Perform other activities which are deemed necessary for the performance of its functions provided under this Proclamation.

2/ The Council shall give its powers stated under Sub-Article (1) of this Article, to the Science, Technology and Innovation Council to be established by law.

## ክፍል ሦስት
## ስታርታፕ እና ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ

**፮. መርህ**

፩/ በስታርታፕ ወይም በስታርታፕ ምኅዳር ገንቢነት ለመንቀሳቀስ የስታርታፕ ወይም የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜን ማግኘት የግዴታ አይደለም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የስታርታፕ ወይም የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜን ማግኘት በዚህ አዋጅ ሥር ከሚቀርቡ ማትጊያዎችና ጥቅሞች ተጠቃሚ ለመሆን ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስታርታፕ ስያሜ ማግኘት እና ብሔራዊ የስያሜ ኮሚቴ መቋቋም

**፯. የስታርታፕ ስያሜ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

፩/ የስታርታፕ ስያሜ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ለስታርታፕ የተሰጠውን የትርጓሜ ይዘቶች ማሟላት አለበት፡፡

፪/ በሕግ ያልተመዘገበና በዚህ አዋጅ ውስጥ የተቀመጡትን የስታርታፕ ትርጓሜ ይዘት የሚያሟላ ግለሰብ ለስታርታፕ ስያሜ፡-

ሀ) ለገበያ የሚያቀርበው ወይም ለማቅረብ ያሰበው ምርት፣ ሒደት ወይም አገልግሎት ባለቤት ስለመሆኑ በማመልከቻው ውስጥ በፊርማ ማረጋገጥ የሚችል፣

ለ) ከካፒታሉ ውስጥ ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነው በመሥራቹ የተያዘ፣ እና

ሐ) የሕዝብ ኩባንያ ያልሆነ መሆን አለበት።

## PART THREE
## STARTUP AND STARTUP ECOSYSTEM BUILDERS DESIGNATION

**6. Principle**

1/ Designation for Startup or startup Ecosystem Builders shall not be mandatory to operate as a Startup or startup Ecosystem Builder.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, being designated as a Startup or startup Ecosystem Builder is a prerequisite to be entitled for the incentives and privileges provided under this Proclamation.

## SUB SECTION ONE
## SATRTUP DESIGNATION AND ESTABLISHING NATIONAL DESIGNATION COMMITTEE

**7. Eligibility for Designation as a Startup**

1/ To be eligible for Designation as a Startup, any person seeking to obtain the designation of a startup shall meet the definitional requirement of a Startup as stipulated under this Proclamation.

2/ An individual who is not registered under the law and meets the definition of a startup as set out in this Proclamation may be designated as a startup:

a) Be the owner of the product, process, or service it provides or intends to provide to the market or be able to demonstrate in its application that it is the owner by a signed affidavit;

b) Have at least Twenty Five percent of its capital held by the founder; and

c) Not be a Public Company.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ቢኖርም የጸና ፈቃድ ያለውና ድርጅቱ ከተመሠረተ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ ማመልከቻውን አቅርቦ ስያሜ ማግኘት ይችላል፡፡

፬/ ስያሜ ያገኘ ስታርታፕ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፰. **<u>የስታርታፕ እና የስታርታፕ ስነምህዳር ገንቢ ምስክር ወረቀት</u>**

፩/ የስታርታፕ ስያሜ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የስታርታፑን ስም፤

ለ) የመሥራቹን ስም፤

ሐ) የስታርታፑን የዕድገት ደረጃ፤ እና

መ) ስታርታፑ የተሰማራበትን ኢንዱስትሪ ወይም ክፍለ ኢኮኖሚ።

፪/ ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ የሚሰጠው የስያሜ ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢውን ስም፤

ለ) የባለቤቱ/ቶቹን ስም፤

ሐ) ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢነት የተሰጠው መደብ፤ እና

መ) የተሰማራበት ክፍለ ኢኮኖሚ።

፫/ የእድገት ደረጃን፣ የብቁነት መስፈርቶች እና የምስክር ወረቀቱ ሊይዝ የሚገባቸው ዝርዝር ጉዳዮች በመመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, an organization that has a valid license and has been established for no more than Five years may submit an application and obtain a designation.

4/ A Designated Startup shall be granted a certificate by the Ministry evidencing its status.

8. **<u>Startup and startup ecosystem builder certificate</u>**

1/ The designation certificate of the startup must meet the following requirement:

a) Name of the Startup;

b) Founder/s' name;

c) Growth stage of the Startup; and

d) Industry or sector of the economy that it is engaged in.

2/ The Designation certificate of the startup ecosystem builder shall meet the following requirements:

a) Name of the Startup Ecosystem Builder;

b) Name of the owner/s;

c) Classification as an Ecosystem Builder; and

d) The sector of the economy that it is engaged in.

3/ The level of development, eligibility requirements, and details that the certificate should contain will be determined by Directives.

**፱. <u>ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩/ ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ የሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት እና አባሪ ሰነዶችን በማሟላት በዲጂታል ስታርታፕ ፕላትፎርሙ በኩል መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ ለስታርታፕ ስያሜ የቀረበው ማመልከቻ በስያሜ ኮሚቴው ተቀባይነት ካገኘ ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን መመዝገብ እና ለአመልካቹ የስያሜ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም ማመልከቻው ተቀባይነትን ካላገኘ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት በመጥቀስ ይህንኑ ለአመልካቹ በሠላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ያስታውቃል፡፡

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስያሜ ኮሚቴው አመልካቹን ለቃለ መጠይቅ እና ስታርታፑ ስለሚያቀርበው ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሒደት ተግባራዊ ገለጻ እንዲያደርግ ሊጠራው ወይም በአካል ተገኝቶ ምልከታ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ የስታርታፕ ስያሜ ለማግኘት ለስያሜ ኮሚቴው የሚቀርብ ማመልከቻ በሠላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

**፲. <u>ብሔራዊ ስያሜ ኮሚቴ ስለ መቋቋም</u>**

፩/ ብሔራዊ የስታርታፕ ስያሜ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴው" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩን ጨምሮ ከ፲፩ የማያንሱ የኮሚቴ አባላት በምክር ቤቱ ይሰየማል፡፡

**9. <u>Application for Designation</u>**

1/ The application for Designation of a Startup shall be done through the Digital Startup Portal by filling out the form prepared for this purpose and providing the attached documents. The details will be determined by the Directive issued by the Ministry.

2/ Where an application to be Designated as a Startup is found acceptable by the Ministry, the Ministry shall register the application, and issue a certificate of Designation to the applicant; provided, however, if the application for Designation is rejected, the Ministry shall notify the applicant in writing by stating the reason for rejection within Thirty working days.

3/ Where relevant, the Designation Committee may call the applicant for an interview or practical presentation about the product, service, or process to be undertaken by the Startup or may conduct an in-person observation.

4/ An application for a Startup Designation filed with the Designation Committee shall be responded within Thirty working days.

**10. <u>Establishment of National Designation Committee</u>**

1/ The National Startup Designation Committee (hereinafter the "Committee") is hereby established.

2/ Not less than 11 committee members, including the Minister shall be appointed by the council.

፫/ የኮሚቴው አባላት፡-

ሀ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና አግባብነት ካላቸው ከሌሎች የመንግሥት ተቋማት፣

ለ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ከጥናትና ምርምር ተቋማት፣

ሐ) ከስታርትአፕ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ ያለው፣

መ) አግባብነት ካለው ከሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የሚውጣጣ ይሆናል፡፡

ሠ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኮሚቴው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ለሥራው የሚያስፈልገውን በጀት ይመድባል፡፡

## ፲፩. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከስታርታፕ እና ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ በዲጂታል ስታርታፕ ፕላትፎርም በኩል የሚቀርብ ማመልከቻን ይቀበላል፣ የአመልካቹን ብቁነት በመመዘን ይወስናል፤ ውጤቱንም ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

ለ) የውስጥ አሰራሩን በተመለከተ የአሰራር ማኑዋል ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የኮሚቴው ዝርዝር ተግባር እና ኃላፊነት በመመሪያ ይወሰናል።

## ፲፪. ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ግዴታዎች

፩/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ፡-

ሀ) በሚያደርገው የንግድ እንቅስቃሴ ተፈጻሚነት ላላቸው ሕጎች ሙሉ ለሙሉ ተገዢ መሆን ፤

3/ Members of the Committee:

a) The Ministry of innovation and technology, the Ministry of labor and skills, the ministry of industry, the Ministry of education, and other relevant government institutions,

b) From higher education institutions and research institutions,

c) Wide-ranging experience in the startup industry,

d) From appropriate civil society institutions.

e) The Ministry of innovation and technology will be the president of the committee.

4/ The Ministry shall allocate the necessary budget for the work.

## 11. Powers and Functions of the Committee

1/ The Committee shall have the following powers and functions:

a) Receive applications from Startups and Startup Ecosystem Builders through the Digital Startup Portal; evaluate and decide on the merits of applicants and submit the result to the Ministry.

b) It may issue an operating manual regarding its internal procedures.

2/ The ministry shall issue a Directive to determine details of powers and functions of the Committee.

## 12. Obligations of a Designated Startup

1/ A Designated Startup shall:

a) Perform its business in full compliance with laws that are applicable to its operation;

ለ) የዕድገት ግቦቹን ለማሳካት ጥረት ማድረግ፤

ሐ) በግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግላዊ የሆነ መረጃ ካልሆነ በስተቀር ከሚኒስቴሩ ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ ሁሉ ስታርታፑን በሚመለከት የሚጠየቀውን መረጃ ማቅረብ፤

መ) ስላገኛቸው ማትጊያዎችና ማትጊያዎቹን በመጠቀም ያስመዘገባቸውን ውጤቶች የሚያሳዩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሠ) በድርጅታዊ ወይም ሕጋዊ መዋቅር፣ ስብጥር፣ ወይም የተሰማራበት የንግድ ሥራ ላይ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ፤

ረ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያገኛቸውን ማትጊያዎች በአግባቡ መጠቀም፤

ሰ) አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች ውስጥ በተደነገጉ ሪፖርት የማድረግ ግዴታዎች መሠረት በአግባቡ የሒሳብ መዝገቦችን መያዝ፤ እና

ሸ) በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚጣሉበትን ማናቸውንም ሌሎች ግዴታዎች መወጣት አለበት፡፡

፪/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ሥር የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣት ካልቻለ ሚኒስቴሩ ግዴዎቹን እየተወጣ አለመሆኑን ባወቀ በዐሥራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ግዴታዎቹን እንዲወጣ ያሳውቀዋል፡፡

b) Strive to achieve its growth objectives;

c) Provide the required information regarding the startup whenever requested by the ministry, except for personal information, subject to the provisions of the personal data protection proclamation;

d) Provide periodical report to the Ministry on incentives received and advancement made by virtue of the incentives;

e) Inform the Ministry of any change in its corporate or legal structure, composition, or business activity within Ten working days to the Ministry;

f) Properly utilize the incentives obtained as per this Proclamation;

g) Maintain proper book of accounts in accordance with reporting obligations provided under the relevant laws of the country; and

h) Fulfill any other obligation imposed on it through this Proclamation, Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation.

2/ If the Designated Startup fails to fulfill the obligations listed under Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall notify the Designated Startup to fulfill its obligations within Fifteen working days of knowing the failure.

፫/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ሥር የተሰጠው ማስጠንቀቂያ በደረሰው በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለጉድለቶቹ ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፫. የስታርታፕ ስያሜ ዕድሳት

፩/ የስታርታፕ ስያሜ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለሁለት ዓመታት የጸና ይሆናል፡፡

፪/ የስታርታፕ ስያሜ ዕድሳት ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ስያሜው የጸና የሆነበት የሁለት ዓመታት ጊዜ ከማብቃቱ ከ፴ የሥራ ቀናት በፊት ነው፡፡

፫/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ለዕድሳት የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው መመሪያዎች ላይ የተቀመጡትን ሌሎች ሰነዶች አባሪ በማድረግ በዲጂታል ስታርታፕ ፕላትፎርም ያቀርባል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የስታርታፕ ስያሜ በማናቸውም ሁኔታ ከስምንት ዓመታት በላይ የጸና ሊሆን አይችልም።

## ፲፬. የስታርታፕ ስያሜ ዕገዳ

፩/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች መወጣት ካልቻለ፤

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያቀርብለት ጥያቄ መሠረት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ካልሰጠ፤

ሐ) ስያሜው የተሰጠባቸውን ተግባራትን ማከናወን ካልቻለ፤ ወይም

3/ The Designated Startup shall rectify the shortcomings within a period of Thirty working days following receipt of the notice stipulated under Sub-Article (2) of this Article.

## 13. Renewal of a Startup Designation

1/ A Startup Designation shall be valid for Two years from the date of issue.

2/ An application for renewal of a Startup Designation shall be submitted Thirty working days prior to the end of the Two years for which the Designation was valid.

3/ The designated startup completes the renewal form and attaches other documents as stipulated in the Directives issued by the Ministry, submitting them on the Digital Startup Platform.

4/ A Startup Designation given under this Proclamation shall not in any way stay valid for more than Eight years.

## 14. Suspension of a Startup Designation

1/ The Designated Startup:

a) Fails to fulfill its obligations under this Proclamation, Regulation and Directives issued there under;

b) Fails to provide timely and accurate information upon request by the Ministry;

c) Fails to carry out the activities for which the Designation was obtained; or

መ) ስያሜውን እንደ ንግድ ድርጅት ያገኘ ስታርታፕ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ካላቀረበ፤ ሚኒስቴሩ የስታርታፑን ስያሜ ሊያግደው ይችላል፡፡

፪/ ስያሜው የታገደበት ስታርታፕ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ማትጊያዎችን ለማግኘት ብቁ አይሆንም፡፡

፫/ የስታርታፕ ስያሜ ሲታገድ ሚኒስቴሩ ለስታርታፑ ባለቤት ስያሜው ስለታገደበት ምክንያትና ለዕገዳው ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን ለማስተካከል በ፴ ቀናት ውስጥ መውሰድ የሚገባውን እርምጃዎች በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

፬/ ለዕገዳው ምክንያት የሆኑ ጉድለቶች በንዑስ-አንቀጽ (፫) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከተስተካከሉ ዕገዳው ተነስቶ ስያሜው የጸና ይሆናል፡፡

፭/ በሚመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት የሚወሰድ የንግድ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕገዳ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የስታርታፕነት ስያሜ የመታገድ ውጤትን ያስከትላል፡፡

፮/ በሚኒስቴሩ የሚደረግ የስታርታፕ ስያሜ ዕገዳ የስታርታፑ የንግድ ፈቃድ ዕገዳ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕገዳ ተደርጎ ሊተረጎም አይገባም፡፡

d) If a startup that has been designated as a commercial enterprise does not submit a renewed business license; The ministry may suspend the startup’s designation.

2/ A Designated Startup whose Designation has been suspended shall not be eligible for the incentives provided under this Proclamation.

3/ When a Startup Designation is suspended, the Ministry shall notify the startup’s owner in writing, the cause of the led suspension and measures that it needs to take within 30 days to rectify the shortcomings that to the suspension.

4/ Where the defects causing the suspension of the Designation is rectified within the time prescribed under Sub-Article (3) of this Article, the suspension shall be lifted and the Designation shall become valid.

5/ The suspension of a business license or competence certificate by a relevant Government organ shall result in the suspension of the Designation without any precondition.

6/ A suspension of Startup Designation by the Ministry shall not be construed as a suspension of a business license or a suspension of a competence certificate of the Designated Startup.

**፲፭. የስታርታፕ ስያሜን መሻር**

፩/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ፡-

ሀ) የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በራሱ ፈቃድ ሲያቆምና የመዝጊያ ሪፖርት ሲያቀርብ፤

ለ) በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ሥር ከሚገኙት የስታርታፕነት የትርጓሜና የብቁነት መመዘኛዎች ውጪ እንዲሆን የሚያደርገውን ውሕደት ወይም ግዢ የሚፈጽም ከሆነ፤

ሐ) ስያሜ የተሰጠው ወይም ስያሜው የታደሰው ሀሰተኛ ሰነድን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ከተረጋገጠ፤

መ) ስያሜውን ላልተፈቀደለት ዓላማ ተጠቅሞበት ከተገኘ፤

ሠ) እንደከሰረ በፍርድ ቤት ከተወሰነ፤

ረ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ስያሜውን ካላሳደሰ፤

ሰ) የስታርታፑ የንግድ ምዝገባ አግባብነት ባለው አዋጅ መሠረት ከተሰረዘ፤ወይም

ሸ) ለስያሜው መታገድ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በ፴ ቀናት ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ ሚኒስቴሩ ስያሜውን ይሽረዋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) (ለ) ፣ (ሐ) እና (መ) መሠረት የስታርታፑን ስያሜ ለመሻር ከመወሰኑ በፊት ስታርታፑ ተቃውሞ ካለው መቃወሚያውን እንዲያቀርብ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**15. Revocation of a Startup Designation**

1/ The Designation of a Startup where:

a) Terminates the business activity by its own choice, provided that a closing report be submitted by the Designated Startup;

b) Undertakes a merger or acquisition that takes it out of the definition and the eligibility requirements of a Startup under this Proclamation or under Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation;

c) It is verified that the Designation was issued or renewed based on falsified document;

d) Utilized the Designation for an unauthorized purpose;

e) Declared bankrupt;

f) Fails to have its Designation renewed under the provisions of this Proclamation;

g) The commercial registration of the Startup is revoked under the relevant Proclamation; or

h) Fails to rectify defects that resulted in the suspension of its Designation within 30 days.The Ministry may revoke the designation.

2/ The Ministry, before deciding to revoke the Designation of a Startup pursuant to Sub- Article (1) (b), (c) and (d) of this Article, shall notify the Startup in writing, to submit its objection in writing, if any.

፫/ ስታርታፑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የሚያቀርበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ማስታወቂያው በደረሰው በ፴ የስራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ማቅረብ ካልቻለ ስያሜው ይሻራል፡፡

**ንዑስ- ክፍል ሁለት**

**የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ**

**፲፮. የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

፩/ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት ብቁ የሚሆነው፡-

ሀ) እንደ አግባብነቱ የንግድ ምዝገባ፣ የንግድ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲኖረው፤

ለ) የስታርታፕ ዕድገት ለመደገፍ ከሚከተሉት ሀብቶች ውስጥ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ሲኖሩት፡-

1) ስታርታፕ ሥራቸውን ማከናወን የሚችሉበት ቦታ፤
2) የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት፤
3) በቂ የፋይናንስ ዐቅም፤
4) ለስታርታፕ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ሒደቶችን ለመሞከር፣ ቅድመ-ምርት (ፕሮቶታይፕ) ለማዘጋጀት፣ ለመግጠም፣ ማረጋገጥ ወይም ምርምር ማከናወን የሚያስችሉ በቂ የኢኖቬሽን መሣሪያዎች፤
5) የልህቀትና የማብቃት ፕሮግራሞች፤
6) ትስስር የመፍጠሪያ ዕድሎች፤ ወይም
7) የሕግና አስተዳደራዊ ድጋፍ።

ሐ) በንግድ ሥራና ፈጠራ ላይ አግባብነት ያለው ብቃት ባላቸው ሰዎች የሚመራ፤ እና

3/ If the objection of a Designated Startup under Sub-Article (2) of this Article is not found to be satisfactory or the Designated Startup fails to submit its objection within Thirty working days of receipt of the notice, the Designation shall be revoked.

**SUB-SECTION TWO**

**DESIGNATION OF STARTUP ECOSYSTEM BUILDERS**

**16. Eligibility for Designation as a Startup Ecosystem Builder**

1/ To be eligible for Designation as a Startup Ecosystem Builder shall:

a) Have a commercial registration, business license or an investment permit, as applicable;

b) Have one or more of the following necessary resources to support the growth of Startups:

(i) Physical space to accommodate Startups;
(ii) Technology infrastructure;
(iii) Adequate financial resources;
(iv) Adequate equipment for innovation to enable Startups test, prototype, install, verify, or research products services or processes;
(v) Mentorship and coaching programs;
(vi) Networking opportunities; or
(vii) Legal and administrative suppor.

c) Be managed by persons with relevant competence on business and innovation; and

መ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተጨማሪ የብቁነት መስፈርቶችን ሲያሟላ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የፋይናንስ ተቋማት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ የምርምርና ማበልጸግ ኤጀንሲዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመሳሰሉት ከዚህ አዋጅ ትግበራ በፊት የስታርታፕ ምህዳር ገንቢነት ሥራ የሚያከናውኑ ተቋማት የሚቀመጡ መሥፈርቶችን በማሟላት በተፋጠነ ሂደት የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ስያሜ የሚሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ይህንኑ ሁኔታ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ከሚኒስቴሩ ይሰጠዋል፡፡

**፲፯. <u>የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩/ ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚወስነውና ለዚሁ ዓላማ የሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት እና አባሪ ሰነዶችን በሟሟላት በዲጂታል ስታርታፕ ፕላትፎርም በኩል መቅረብ ይኖርበታል።

፪/ ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ የቀረበው ማመልከቻ በኮሚቴው ተቀባይነት ካገኘ ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን መመዝገብ እና ለአመልካቹ ስያሜ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

d) Other additional eligibility criteria that may be determined by the Ministry through a Directive.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall facilitate the accelerated process of obtaining the designation of Startup Ecosystem Developer by financial institutions, higher education institutions, technical and vocational education and training institutions, research and development agencies, non-governmental organizations, and other institutions that have been engaged in the development of startup ecosystems prior to the implementation of this Proclamation; the details shall be determined by a Directive issued by the Ministry.

3/ A Designated Startup Ecosystem Builder shall be granted by the Ministry a certificate evidencing its status.

**17. <u>Application for Startup Ecosystem Builder Designation</u>**

1/ The application for Designation of Startup Ecosystem Builder shall be done through the Digital Startup Portal by filling the prescribed form and attaching documents specified on the platform.

2/ Where an application to be designated as a Startup Ecosystem Builder is found acceptable by the committee, the Ministry shall register the application and issue a certificate of Designation to the applicant.

፫/ ማመልከቻው ተቀባይነትን ካላገኘ ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት በመጥቀስ ይህንኑ ለአመልካቹ በሠላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው አመልካቹን ለቃለ መጠይቅ ሊጠራው ይችላል፡፡

፭/ ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በሠላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ማግኘት አለበት።

፮/ ሚኒስቴሩ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ማመልከቻ የሚቀርብበትንና የሚገመገምበትን ስርዓት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

**፲፰. <u>ስያሜ የተሰጣቸው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ግዴታ</u>**

፩/ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ፡-

ሀ) አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች ውስጥ በተደነገገው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ መሠረት የሒሳብ መዝገቦችን መያዝ፤

ለ) ተፈጻሚነት ያላቸውን የሀገሪቱን ሕጎች ማክበር እና ተገዥ መሆን ፤

ሐ) አስፈላጊውን የብቃትና የጥራት ደረጃ መመዘኛ ማሟላት፤

መ) ለኢኖቬሽንና ለቴክኖሎጂ ዕድገት አስቻይ የሆነ ከባቢን መፍጠርና ማመቻቸት፤

ሠ) ለስታርታፕ እንዲቀርቡ የሚዘጋጁትን ማትጊያን አግባብነት ያለው በማድረግ ፍትሐዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ማከፋፈል፤

3/ If the application for Designation is rejected, the Ministry shall notify the applicant in writing stating the reason for rejection within thirty working days.

4/ Where relevant, the Ministry may call the applicant for an interview.

5/ An application for a Startup Ecosystem Builder Designation shall be reviewed and responded within Thirty working days.

6/ The Ministry may issue a Directive that will be utilized to evaluate applications for Designation as a Startup Ecosystem Builder.

**18. <u>Obligation of Designated Startup Ecosystem Builders</u>**

1/ A Designated Startup Ecosystem Builder shall:

a) Keep its book of accounts in accordance with reporting obligation provided under the relevant laws of the country;

b) Respect and abide by the applicable laws of the country;

c) Fulfill the necessary competence and quality standard requirement;

d) Create and facilitate an enabling environment for the enhancement of innovation and technology;

e) Distribute Startup incentives channeled to it, on the basis of merit in a fair and efficient manner;

ረ) ስታርታፕ የሚመለከቱ መረጃዎችንና ማስታወቂያዎችን ዲጂታል የስታርታፕ ፕላትፎርሙን በመጠቀም ማስተላለፍ፤

ሰ) የስታርታፕ ምኅዳሩን ለማሳደግ ከተቀመጡ ዓላማዎች ውጪ ማበረታቻዎችን አለመጠቀም፤ እና

ሸ) የስታርትአፕ ምህዳር ገንቢ በኩል የተደረገ ማንኛውም ለውጥ ለሚኒስቴሩ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ሥር የተቀመጡትን ግዴታዎች ካልተወጣ ሚኒስቴሩ ጉድለቱን ባወቀ በ፴ ቀናት ውስጥ ስያሜ ለተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ግዴታዎቹን እንዲወጣ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለማስጠንቀቂያው ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ ለስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ የሚሆን የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፱. <u>የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ዕድሳት</u>

፩/ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ለአምስት ዓመት የጸና ይሆናል፡፡

f) To the extent it is possible and without interfering with its normal operations, use the Digital Startup Portal to disclose information and announcements relevant to Startups;

g) Not use the incentive for purposes other than the development of the Startup Ecosystem in line with the objectives they are established for; and

h) Provide information to the Ministry within 15 days on any change of its business operation or objective.

2/ If the Designated Startup Ecosystem Builder fails to fulfill the obligations listed under Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall notify the Designated Startup Ecosystem Builder to fulfill its obligations within 30 days of knowing the failure.

3/ The Designated Startup Ecosystem Builder shall respond to the notice within a period of Thirty working days following receipt of the notice stipulated under Sub-Article (2) of this Article.

4/ The Ministry may issue a Directive for the proof of qualification of Startup Ecosystem Builder.

## 19/ <u>Renewal of a Startup Ecosystem Builder Designation</u>

1/ A Startup Ecosystem Builder Designation Shall be valid for Five years.

፪/ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ የዕድሳት ማመልከቻ ስያሜው ከሚያበቃበት ጊዜ ሠላሳ የሥራ ቀናት አስቀድሞ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ለዕድሳት የተዘጋጀውን ቅጽ መሙላትና በዲጂታል የስታርታፕ ፕላትፎርም ላይ የተቀመጡትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

## ፳. የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ ዕገዳ

፩/ ሚኒስቴሩ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች መወጣት ካልቻለ፣

ለ) ሚኒስቴሩ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ካልሰጠ፣

ሐ) ስያሜው የተሰጠባቸውን ተግባራት ማከናወን ካልቻለ፣

መ) ጥሰቶችን ከፈጸመ፣ወይም

ሠ) የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ ካልቻለ፣ የስታርታፑን ስያሜ ሊያግደው ይችላል፡፡

፪/ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ በሚታገድበት ጊዜ ሚኒስቴሩ ስያሜው የታገደበትን ምክንያትና በ፴ ቀናት ውስጥ ጉድለቶቹን ለማስተካከል መውሰድ ያለበትን እርምጃዎች የሚያስረዳ ማስጠንቀቂያ ለስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው መስጠት አለበት፡፡

2/ An application for renewal of a Startup Ecosystem Builder Designation shall be submitted Thirty working days prior to the Designation was valid.

3/ The Designated Startup Ecosystem Builder shall fill in the form prepared for the purpose of renewal and submit any other documents specified in the Digital Startup Portal.

## 20. Suspension of a Startup Ecosystem Builder Designation

1/ The Ministry may suspend a Startup Ecosystem Builder Designation where the Designated Startup Ecosystem Builder:

a) Fails to fulfill its obligations under this Proclamation, Regulations and Directives issued there under;

b) Fails to provide timely and accurate information upon request by the Ministry;

c) Fails to carry out the activities for which the Designation was obtained;

d) Commits other similar offences; or

e) If a renewed business license cannot be provided.

2/ When a Startup Ecosystem Builder Designation is suspended, the Ministry shall notify the holder of the Designation in writing, the cause of the suspension and measures that it needs to take within 30 days to rectify the shortcomings that led to the suspension.

፫/ ለስያሜው መታገድ ምክንያት የሆኑት ጉድለቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ሥር በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ከተስተካከሉ ዕገዳው ተነስቶ ስያሜው የጸና ይሆናል፡፡

፬/ በሚመለከተው የመንግስት አካል የሚደረግ የንግድ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕገዳ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የስያሜን ዕገዳ ያስከትላል፡፡

፭/ በሚኒስቴሩ የሚደረግ የስያሜ ዕገዳ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው የንግድ ፈቃድ ዕገዳ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዕገዳ ተደርጎ ሊተረጎም አይገባም፡፡

**፳፩. <u>የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስያሜ መሻር</u>**

፩/ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ፡-

ሀ) በራሱ ፈቃድ የንግድ እንቅስቃሴውን ሲያቆም፤

ለ) ስያሜው የተሰጠው ወይም የታደሰው ሀሰተኛን ሰነድ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ስያሜውን ላልተፈቀደ ዓላማ ተጠቅሞበት ከተገኘ፤

መ) እንደ ከሰረ በፍርድ ቤት ከተወሰነ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ስያሜውን ማሳደስ ካልቻለ፤

ረ) አግባብነት ባለው አዋጅ መሠረት የንግድ ምዝገባው ወይም የንግድ ፈቃዱ ከተሰረዘ፤ ወይም

3/ Where the defects causing the suspension of the Designation are rectified within the time prescribed under Sub-Article (2) of this Article, the suspension shall be lifted, and the Designation becomes valid.

4/ The suspension of a business license or a competency certificate by the relevant Government organ shall result in the suspension of the Designation without any precondition.

5/ A suspension of a Startup Ecosystem Builder Designation by the Ministry shall not be construed as a suspension of a business license or a competency certificate of the Designated Startup Ecosystem Builder.

**21. <u>Revocation of a Startup Ecosystem Builder Designation</u>**

1/ The designation of a Startup Ecosystem Builder where:

a) Terminates the business activity by its own choice;

b) It is verified that the Designation was issued or renewed based on falsified document;

c) Utilized the Designation for an unauthorized purpose;

d) Declared by court as bankrupt;

e) Fails to have its Designation renewed under the provisions of this Proclamation;

f) If the business registration or business license is revoked in accordance with the relevant Proclamation; or

ሰ) ስያሜው ታግዶ ከሆነ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ለስያሜው መታገድ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን ማረም ካልቻለ፤ ሚኒስቴሩ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢውን ስያሜ ይሽራል፡፡

፪/ ስያሜው የታገደው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተጠቀሱት ምክንያቶች መሠረት ከሆነ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው አስገዳጅ የመዝጊያ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) መሠረት የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢን ስያሜ ለመሻር ከመወሰኑ በፊት ስያሜ ለተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ተቃውሞ ካለው ይህንኑ በጽሑፍ እንዲያቀርብ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት።

፬/ ስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው የሚያቀርበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው ማስጠንቀቂያው በደረሰው በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ማቅረብ ካልቻለ ስያሜው ይሰረዛል፡፡

## ፳፪. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

፩/ ከስታርታፕና ስታርታፕ ምሕዳር ገንቢ ስያሜ፣ ስያሜ ማገድ እና ስያሜ መሰረዝን ጨምሮ ከስታርታፕና ስታርታፕ ምሕዳር ገንቢ የሚቀርቡ ማናቸውንም ቅሬታዎች የሚፈታ ከ፯ ያላነሰ አባላት ያሉት አካታችና ገለልተኛ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ (ከዚህ ቀጥሎ የቅሬታ ኮሚቴ እየተባለ የሚጠቀስ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

g) If the designation has been suspended, if it fails to correct the deficiencies that led to the suspension of the designation within the given time period. The Ministry may revoke the designation of a Startup Ecosystem Builder.

2/ If the designation is revoked for the reasons mentioned in Sub-Article (1) of this Article, the Startup Ecosystem Builder is required to submit a necessary exit report.

3/ The Ministry, before deciding to revoke the Designation of a Startup Ecosystem Builder pursuant to Sub-Article (1) (b), (c) and (d) of this Article, shall notify the Designated Startup Ecosystem Builder in writing, to submit its objection in writing, if any.

4/ If the objection of the Designated Startup Ecosystem Builder is not found to be satisfactory or the Designated Startup Ecosystem Builder fails to submit its objection within Thirty working days of receipt of the notice, the Designation shall be revoked.

## 22. Establishment of grievance committee

1/ An inclusive and independent grievance committee (hereinafter referred to as the Grievance committee) consisting of no less than 7 members is hereby established to resolve any grievance filed against startups and startup ecosystem builders, including the designation, suspension and cancellation of designation.

፪/ የቅሬታ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሚንስትሩ ይሆናል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ የቅሬታ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነትን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**ክፍል አራት**

**ስያሜ ለተሰጣቸው ስታርታፖች ስለሚሰጡ ማትጊያዎች**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**ግራንት እና የዋስትና ፈንድ**

**፳፫. የስታርታፕ ግራንት ፕሮግራም መቋቋም**

፩/ ስያሜ ያላቸውን ስታርታፕ ለመደገፍ የስታርታፕ ግራንት ፕሮግራም (ከዚህ በኋላ “ግራንት” እየተባለ የሚጠራ) የተቋቋመ ሲሆን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሚኒስቴሩ የሚተዳደር ይሆናል፡፡

፪/ ግራንቱን ስራ ለማስጀመር የሚያስፈልግ በጀት በመንግስት ይሸፈናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግራንቱ ገንዘብ፡-

ሀ) ከልማት አጋሮች የሚገኝ ድጋፍ፤ እና

ለ) የገንዘብ ሚኒስቴር የግራንቱ አካል እንዲሆን ከሚያጸድቀው ማንኛውም ሌሎች ምንጮች ሊገኝ ይችላል፡፡

፬/ የገንዘብ ሚኒስቴር የግራንቱን አመራር፣ አስተዳደርና አሠራር የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡

2/ The complaints committee shall be accountable to the Ministry.

3/ The Ministry shall issue detailed Directive regarding the functions and responsibilities of the complaints committee.

**PART FOUR**

**INCENTIVES FOR DESIGNATED STARTUPS**

**SUB-SECTION ONE**

**GRANT AND GUARANTEE FUND**

**23. Establishment of a Startup Grant Program**

1/ A Startup Grant Program (here under the “Grant”) is hereby established to support Designated Startups and shall be administered by the Ministry pursuant to a Directive to be issued by the Ministry of Finance.

2/ The budget required to launch the grant will be covered by the government.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the funds of the Grant may consist of:

a) Support made by development partners; and

b) Any other resources approved by the Ministry of Finance to be a part of the Grant.

4/ The Ministry of Finance shall issue a Directive as to the management, administration, and operation of the Grant.

**፳፬. <u>የግራንቱ ዓላማዎች</u>**

፩/ ግራንት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመጀመሪያ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ያሉ ስያሜ ለተሰጣቸው ስታርታፕ ስያሜ ለተሰጠበት ምርት ወይም አገልግሎት የምርምር ስራ ወደ ሥራ ማስገቢያ፣ ልማትና የንግድ ስራ ሂደት ጋር የሚያያዙ ወጪዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ግራንቱን ለሚከተሉት የግል ወይም የንግድ ተግባራት ማዋል የተከለከለ ነው፡-

ሀ) ስያሜ ከተሰጠው ስታርታፕ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የግል ወጪዎች፤

ለ) በግራንቱ ማመልከቻ ላይ ያልተጠቀሱ የንግድ እንቅስቃሴዎች፤

ሐ) የግል ወይም የድርጅት ዕዳዎችን መልሶ ለመክፈል፤

መ) ስያሜው ከተሰጠበት ዓላማ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች፤

ሠ) ስያሜ ከተሰጠው ስታርታፕ ምሥረታ፣ ትግበራ፣ ልማትና የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር የማይገናኝ የሪል እስቴት ወይም የሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዥ፤ እና

ረ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተከለከለ ማንኛውም ሌላ ተግባር።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሠረት የግራንቱን ገንዘብ በማከፋፈል የሚሳተፉ ስያሜ ያላቸው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ግራንቱን ለግላቸው ወይም ለንግድ ተግባራቸው መጠቀም አይችሉም፡፡

**24. <u>Objective of the Grant</u>**

1/ The Grant shall be used to cover costs related to the research, implementation, development, and operation (commercialization) of the Designated Startups that is in the initial stages of development to be determined through a Directive by the Ministry.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the use of the Grant for the following personal or commercial activities are prohibited:

a) Personal expenses unrelated to the Designated Startup’s operation;

b) Commercial activities not specified in the Grant application;

c) Repayment of personal or corporate debts;

d) Investments activities unrelated to the objectives of the Designation;

e) Purchase of real estate or other fixed assets which are not relevant to the establishment, implementation, development, and operation of the Designated Startup; and

f) Any other activity prohibited by the Directive issued by the ministry.

3/ Designated Startup Ecosystem Builders that take part in the Distribution of_the Grant as per Article 24, of this Proclamation, shall not use the Grant for their own personal or commercial activities.

**፳፭. ግራንት ስለ ማከፋፈል**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ-አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ ግራንት በቀጥታ ወይም ስያሜ በተሰጠው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ በኩል ግራንቱን ማሰራጨት ወይም ማከፋፈል ይችላል።

፪/ ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ የሚሰጠው ዝቅተኛና ከፍተኛ የግራንት ገንዘብ መጠን በዚህ አዋጅ ላይ የተቀመጡትን የግራንቱን ዓላማዎችና የገንዘብ ሚኒስቴር የግራንቱን አስተዳደር በሚመለከት የሚያወጣውን መመሪያ ከግምት በማስገባት በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫/ ግራንት የተቀበለ ስያሜ ያለው ስታርታፕ ለአንድ ዓመት ለሚሆን ጊዜ ለሌላ ግራንት ማመልከቻ ማቅረብ አይችልም፡፡

፬/ ስያሜ ያለው ስታርታፕ ውስጥ ሃያ አምስት በመቶ ወይም ከዚያ የሚበልጥ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸውና በሌላ ስያሜ ያለው ስታርታፕ በኩል ግራንትያገኙ ግለሰብ መሥራቾች ወይም የጋራ-መሥራቾች ለአንድ ዓመት ለሚቆይ ጊዜ ለሌላ ግራንትማመልከቻ ማቅረብ አይችሉም፡፡

፭/ ግራንት ያገኘ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ሒሳብ በሕግ ከተጣራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) እና (፬) የተቀመጡት ገደቦች ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

፮/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ በተመሳሳይ የፈጠራ ሀሳብ ከአንድ ጊዜ በላይ ለግራንት ማመልከት አይችልም።

**25. Distribution of the Grant**

1/ Notwithstanding of the provision of Sub-Article (4) of Article 22 of this Proclamation, the ministry may distribute or distribute the grant to the designated startup grantee directly or through the designated startup ecosystem developer.

2/ The minimum and maximum amount of the Grant distributed to a Designated Startup shall be determined by the Ministry taking into consideration the objective of the Grant stated in this Proclamation and the provisions of the Directive to be issued by the Ministry of Finance for the management of the Grant.

3/ A Designated Startup who has received a Grant shall not be entitled to reapply for another Grant for a period of One year.

4/ Individual founders or co-founders with Twenty Five percent or more ownership interest in a Designated Startup and who has already secured a Grant through another Designated Startup shall not be eligible to apply for another Grant for a period of One year.

5/ If a Designated Startup that has already secured a Grant is legally liquidated, the restriction under Sub-Article (3) and (4) of this Article shall not be applicable.

6/ A Grant shall not be applied for the same idea and by the same Designated Startup twice.

፯/ ለግራንት በሚያመለክቱበት ወቅት መሥራቾች የባለቤትነት ድርሻ ወይም ከፍተኛ የሥራ አመራር ሚና የያዙባቸውን ስያሜ የተሰጣቸው ስታርታፕ በሙሉ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፰/ ስያሜ በተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ በኩል የሚከፋፈለው ከፍተኛ የገንዘብ ጣሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር ይወሰናል።

፱/ የግራንቱ ተጠቃሚዎችና ግራንቱን የሚያከፋፍሉ ስያሜ ያላቸው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ስለግራንቱ ክፍፍልና አጠቃቀም ለሚኒስቴሩ በየጊዜው ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

**፳፮. <u>የስታርታፕ እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ብሔራዊ የብድር ዋስትና ፈንድ</u>**

፩/ የስታርታፕ እና ምህዳር ገንቢ ብሔራዊ የብድር ዋስትና ፈንድ (ከዚህ በኋላ "የዋስትና ፈንድ" እየተባለ የሚጠቀስ) ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዋስትና ፈንዱ ተጠቃሚዎች፡-

ሀ) ስያሜ ያላቸው ስታርታፖች፣

ለ) ስያሜ ያላቸው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢዎች፣ እና

ሐ) ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች፣ ሲሆኑ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ለስታርታፕ የብድር ተደራሽነትን የማሳደግ ዓላማ ያለው ነው፡፡

፫/ የዋስትና ፈንዱ ተቆጣጣሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፡፡

7/ At the time of Grant application, founders must disclose all Designated Startups in which they hold ownership interests or significant management roles.

8/ The maximum amount that can be distributed by a Designated Startup Ecosystem Builder to Designated Startups shall be determined by the Ministry of Finance.

9/ The beneficiaries and the distributing Designated Startup Ecosystem Builder of the Grant shall have a periodical reporting obligation to the Ministry regarding the distribution and the usage of the Grant on a timely basis.

**26. <u>National Credit Guarantee Fund for Startups and Ecosystem Builders</u>**

1/ The National Credit Guarantee fund (hereinafter the "Guarantee fund") is hereby established.

2/ Beneficiaries of the Guarantee fund shall be:

a) Designated Startups,

b) Designated Startup Ecosystem Builders, and

c) Micro, Small and Medium Enterprises with the aim of increasing the level of credit access to Startups and Micro, Small and Medium Enterprise.

3/ The supervisory authority of the Guarantee fund shall be the National Bank of Ethiopia.

፬/ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለዋስትና ፈንዱ ብቁ የሚሆኑ ስታርታፖችን፣ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢዎችን፣ እንዲሁም ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞችን በሚያወጡት መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ይለያሉ።

፭/ መንግስት የዋስትና ፈንዱን ለማስጀመር የመመስረቻ ካፒታል ይመድባል፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊው ፈቃድ ሲገኝ የዋስትና ፈንዱን የሚያቀርባቸውን ዋስትና የመስጠት ስልጣን ሊያሰፋ ይችላል፡፡

፯/ የዋስትና ፈንዱ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የገቢ ምንጭ፣ አመራር፣ አስተዳደር፣ የሥራ እንቅስቃሴና ሌሎች ዝርዝሮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፳፯. <u>የዋስትና ፈንድ ዓላማዎች</u>

የዋስትና ፈንድ ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች እና ስያሜ ላላቸው ስታርታፕ እና ስያሜ ላላቸው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ የብድር ዋስትና መስጠት፤

፪/ ሀብቶቹን ኢንቨስት ማድረግ፤ እና

፫/ ወደ ዋስትና ፈንዱ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው የፋይናንስ ተቋማት በብድር ዋስትናዎቹ መሠረት ለሚያቀርቧቸው የክፍያ ይገባኛል ጥያቄዎች ተገቢውን ክፍያ መፈጸም፤

4/ The Ministry of Innovation and Technology; and the Ministry of Labor and Skills, and the Ministry of Industry shall establish and promulgate applicable criteria governing eligibility for participation in the guarantee scheme, to startups, and startup ecosystem builders; and micro, small, and medium enterprises, respectively, in accordance with the provisions of this Proclamation.

5/ The Government shall make an initial capital to establish the Guarantee fund.

6/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the Guarantee fund mandate to provide guarantees can be expanded when the necessary authorization is provided by the National Bank of Ethiopia.

7/ The organizational structure, source of income, management, administration, operations and other details of the guarantee fund shall be determined by a Regulation issued by the council of Ministers.

## 27. <u>Objectives of the Guarantee Fund</u>

The objective of the Guarantee fund is as follows:

1/ Issue credit guarantees to Designated Startups, Designated Startup Ecosystem Builders, and Micro, Small and Medium Enterprises;

2/ Invest its assets; and

3/ Effect payments to admitted financial institutions on claims made in accordance with the credit guarantees;

**፳፰. የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች ግዴታ**

፩/ ሁሉም የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች የብድሩን ሙሉ መጠን በብድር ስምምነቱ ደንብና ሁኔታዎች መሠረት የመመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

፪/ ተጠቃሚዎች ብድሩን በብድር ማመልከቻው ላይ ለተጠቀሱት ዝርዝር ዓላማዎች ብቻ የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፡፡

**፳፱. ክልከላ**

፩/ የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች የብድሩን ገንዘብ በብድር ስምምነቱ ላልተፈቀዱ ወጪዎች ማዋል አይችሉም፡፡

፪/ በዋስትና ፈንድ ዋስትና የተሰጠውን ብድር ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት መልሶ አለመክፈል የተከለከለ ነው፡፡

፫/ በዋስትና ፈንድ ሥር ያለባቸውን ዕዳ ሆን ብለው የማይከፍሉ ተጠቃሚዎች ለአሥር ዓመታት ከዋስትና ሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም፡፡

፬/ ሆን ብሎ ዕዳን ያለመክፈል እና መልሶ የመክፈል ግዴታን ያለመወጣት ውጤቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ልዩ ልዩ ማትጊያዎች**

**፴. የግብር ማትጊያዎች**

፩/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ አግባብነት ባላቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሕጎች ውስጥ የተዘረዘሩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

**28. Obligation of Guarantee Fund Beneficiaries**

1/ All beneficiaries of the Guarantee fund shall be obliged to repay the full amount of the loan according to the terms and conditions of the loan agreement.

2/ Beneficiaries shall utilize the loan for the specific purposes stated in the loan application.

**29. Prohibition**

1/ Beneficiaries of the Guarantee fund are prohibited from using the proceeds of the loan for expenses not related to what has been authorized by the loan agreement.

2/ Intentional or negligent default to repay a loan that is guaranteed under the Guarantee fund is strictly prohibited.

3/ Beneficiaries who intentionally defaulted on repayment under the Guarantee fund shall not be allowed to benefit from the Guarantee fund for the period of Ten years.

4/ Consequences related with intentional default and failure to repay loan shall be determined by the Regulation to be issued by the Council of Ministers.

**SUB-SECTION TWO**

**MISCELLANEOUS INCENTIVES**

**30. Tax Incentives**

1/ A Designated Startup shall be a beneficiary of the incentives specified under the relevant Investment Incentives laws.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስያሜ ያለው ስታርታፕ የስያሜው ዘመን ከማብቃቱ በፊት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

ሀ) ከማንኛውም ገቢ ግብር፤

ለ) ለባለ አክሲዮኖች በሚከፋፈል የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚጣል የገቢ ግብር፤ እና

ሐ) በከፋዩ ተቀንሶ ከሚቀር ግብር ነፃ ይሆናል፡፡

፫/ ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ የሚሰጥና ምንም ዓይነት ወደ ባለቤትነት ድርሻ ወይም ወደ ዕዳ የመለወጥ ዕድል የሌለው ማንኛውም የግራንት ማበረታቻ፣ ስጦታ፣ ልገሳ ወይም ተመሳሳይ የመዋጮ ዓይነት ለገቢ ግብር አዋጁ ዓላማ ገቢ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡

፬/ ስያሜ በተሰጠው ስታርታፕ ሠራተኛ ሆነው የተቀጠሩ የውጪ ዜጎች የስታርታፕ ስያሜው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት በመቀጠር የሚያገኙት ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፡፡

፭/ ከግብር ነፃ ለመደረግ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሚኒስቴሩ ተረጋግጠው ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ ይኖርባቸዋል።

**፴፩. <u>የስታርታፕ ኪሳራን ወደፊት ስለማሸጋገር</u>**

፩/ ማንኛውም ስያሜ ያለው ስታርታፕ በገቢ ግብር ነፃ በሆነበት ዘመን ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ይህ ኪሳራ የግብር እፎይታው ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው ጊዜ የእፎይታውን ዘመን ግማሽ ለሚሆን የግብር ጊዜ ኪሳራውን ለማሸጋገር ይችላል።

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a designated startup before the expiration of the designation, in accordance with the Directive issued by the Ministry of Finance:

a) From Any income tax;

b) From income tax on dividend distributed to shareholders; and

c) From withholding tax; It will be exempt.

3/ Any form of grant, incentive, gift, donation, or similar type of contribution to a Designated Startup with no possibility of equity or conversion to debt shall be considered, for the purpose of the Income Tax Proclamation, as a non-income proceed and shall not be taxed.

4/ The income earned by foreign nationals employed as employees of a designated startup before the expiration of the startup designation period shall be exempt from income tax.

5/ The application for eligibility to tax exemption shall be verified by the Ministry and shall be submitted for approval to the Ministry of Finance.

**31. <u>Loss Carry Forward by Startups</u>**

1/ A Designated Startup who has incurred a loss within the period of income tax exemption, this loss can be carried forward to a tax period equal to half of the exemption period after the tax exemption period ends.

፪/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ለአንድ የግብር ዓመት ኪሳራ ካጋጠመው ግብር ከፋዩ የዚህን ኪሳራ መጠን ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ያስተላልፈዋል፡፡ ኪሳራውም የሚቀጥለው ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሲሰላ እንደ ወጪ ይያዛል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ኪሳራን ወደፊት ማስተላለፍ የሚፈቀደው ለሦስት ዓመታት ብቻ ነው።

**፴፪. በባለሀብት ወደፊት የሚተላለፍ ኪሳራ**

፩/ ስያሜ በተሰጠው ስታርታፕ ውስጥ የባለቤትነት ድርሻ ለማግኘት ገንዘብ ኢንቨስት ካደረገ በኋላ ስያሜ ባለው ስታርታፕ ውስጥ ገንዘቡን የከሰረ ባለሀብት በራሱ የሒሳብ መግለጫ ውስጥ ይህን ኪሳራ መቶ በመቶ ተቀናሽ የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ ኪሳራን ወደፊት ማስተላለፍ የሚፈቀደው ለሁለት ዓመት ብቻ ነው፡፡

**፴፫. ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ ከቀረጥ ነፃ የመሆን መብት**

፩/ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ሊያስገባ ይችላል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ትግበራ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፑ ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ያሰባቸውን የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር ለገንዘብ ሚኒስቴር በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2/ If a Designated Startup has a loss for a tax year, the taxpayer shall carry the amount of the loss forward to the next following tax year and the loss shall be allowed as a deduction in computing the taxpayer’s taxable income for the following year.

3/ The loss to be carried forward in accordance with Sub-Article (1) and (2) of this Article shall only be carried forward for Three years.

**32. Loss Carry Forward by Investor**

1/ An Investor that has invested money in a Designated Startup in return for equity and subsequently lost money in the Designated Startup should be eligible to deduct one hundred percent of the loss incurred on its own financial statement.

2/ The loss to be carried forward in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall only be carried forward for Two years.

**33. Duty Free Privilege for Designated Startups**

1/ A Designated Startups may import duty free capital goods necessary for its operation.

2/ For the implementation of Sub-Article (1) of this Article, a Designated Startup shall submit, the list of capital goods to be imported duty-free and get approval of same from the Ministry of Finance.

፫/ ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ማትጊያ ተጠቃሚ የሆነ ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ የካፒታል ዕቃዎቹን ከአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ ከገዛ የጉምሩክ ኮሚሽን እነዚህን ዕቃዎች ለማምረት ጥቅም ላይ በዋሉት ግብዓቶች ላይ የተከፈሉትን ቀረጦችና ታክሶች ለከፋዩ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## ፴፬. <u>ስያሜ ለተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ከቀረጥ ነፃ የመሆን መብቶች</u>

፩/ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ የስታርታፕ ምኅዳር አዲስ ፋሲሊቲ ለመገንባት ወይም ተገንብቶ ያለን ፋሲሊቲ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ትግበራ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢው ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ያሰባቸውን የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር ለገንዘብ ሚኒስቴር በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፫/ ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ማትጊያ ተጠቃሚ የሆነ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ የካፒታል ዕቃዎቹን ከሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ ከገዛ የጉምሩክ ኮሚሽን እነዚህን ዕቃዎች ለማምረት ጥቅም ላይ በዋሉት ግብዓቶች ላይ የተከፈሉትን ቀረጦችና ታክሶች ለከፋዩ ተመላሽ ያደርጋል ፡፡

፬/ ስያሜ የተሰጠው የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ በዚህ አዋጅ ሥር የሚቀርቡ ማበረታቻዎችን ለማግኘት በሚያመለክትበት ጊዜ ሁሉ የጸና ስያሜ ሊኖረው ይገባል፡፡

3/ If a Designated Startup entitled to duty-free incentive buys capital goods from a local manufacturing industry, the duties and taxes paid on inputs for the manufacturing of such goods shall be refunded by the Customs Commission to the payer.

## 34. <u>Duty Free Privilege for Designated Startup Ecosystem Builders</u>

1/ A Designated Startup Ecosystem Builder may import duty free capital goods necessary for the establishment of a new facility or the expansion or upgrading of an existing facility.

2/ For the implementation of Sub-Article (1) of this Article, a Designated Startup Ecosystem Builder shall submit, the list of capital goods to be imported duty-free and get approval of same from the Ministry of Finance.

3/ If a Designated Startup Ecosystem Builder entitled to a duty-free incentive buys capital goods from a local manufacturing industry, the duties and taxes paid on inputs for the manufacturing of such goods shall be refunded by the Customs Commission.

4/ A designated startup ecosystem builder must have a valid designation at all times when applying for incentives under this Proclamation.

፭/ አንቀጽ ፴፫ እና አንቀጽ ፴፬ ላይ የተደነገጉትን ከቀረጥ ነፃ የመሆን መብቶችን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ግዴታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## የስታርታፕ የፈንዶች ፈንድ

### ፴፭. የስታርታፕ የፈንዶች ፈንድ መቋቋም

፩/ የስታርታፕ የፈንዶች ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራ) በኢትዮጵያ መንግስትና በግሉ ዘርፍ ትብብር እንደ ንግድ ድርጅት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን የውጭ ባለሀብቶችንም ሊያካትት ይችላል፡፡

፪/ መንግሥት በፈንዱ ውስጥ የሚኖረው ድርሻ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚያዝ ይሆናል፡፡ በመንግሥት የሚያዘው የባለቤትነት ድርሻ መጠን በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ደንብ ቁጥር ፬፻፹፯/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፱ መሠረት የሚወሰን ይሆናል።

፫/ ፈንዱ የሚተዳደረው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የዳይሬክተሮች ቦርድ በውድድር በተመረጠ የግል የፈንድ አስተዳዳሪ ይሆናል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ህግ፣ በካፒታል ገበያ አዋጅ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተደነገጉ ተገቢነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5/ The obligation set forth in other relevant laws shall apply to the duty free exemption rights provided in Article 33 and 34 of this proclamation.

## PART FIVE

## STARTUP FUND OF FUNDS

### 35. Establishment of Startup Fund of Funds

1/ The Startup Fund of Funds (hereinafter the "Fund") is hereby established as a commercial enterprise by the Government of Ethiopia in partnership with the private sector and may include Foreign Investors.

2/ The Government's interest of the Fund of Funds shall be held by the Ethiopian Investment Holdings. The amount of ownership interest held by the government will be determined in accordance with Article 9 of Ethiopian Investment Holdings Regulation No. 487/2022.

3/ The fund will be managed by a private fund manager selected through a competitive process by the board of directors of Ethiopian investment holding.

4/ Notwithstanding of this Article, the relevant provisions of the Commercial Code, the capital markets Proclamation and other relevant laws shall apply.

**፴፮. <u>የፈንዱ ዓላማ</u>**

፩/ የፈንዱ ዓላማ ስያሜ ባገኙ ስታርታፕ ላይ ኢንቬስት በሚያደርጉ ሌሎች ፈንዶች ላይ ካፒታሉን ኢንቬስት ማድረግ ነው፡፡

፪/ የውጪ ስታርትአፕ ገንቢ ምህዳር ኢንቨስትመንት ፍሰትን እና ዓለም አቀፍ ትሥሥርንና ድጋፎችን ማሳደግ ነው፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ተገቢ የፈንዱ ዓላማዎች በፈንዱ አስተዳዳሪ ሊወሰን ይችላል።

**36. <u>Purpose of the Fund</u>**

1/ The purpose of the Fund of Funds shall be to invest its capital on other Funds that invest on designated Startups.

2/ Increasing the flow of foreign venture capital investment and international connections and support into the domestic startup ecosystem.

3/ Subject to Sub-Article (1) of this Article, other purposes of the Fund may be determined by the Fund Manger as deemed appropriate.

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የቁጥጥር ማዕቀፍ</u>

## <u>PART SIX</u>
## <u>REGULATORY SANDBOX</u>

**፴፯. <u>የሙከራ ፈቃድና ክትትል</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ፈጠራን ለማበረታታትና በስታርታፕ ለገበያ የሚቀርቡ አዳዲስ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችንና ሒደቶችን ለመሞከርና ለማስተዋወቅ እንዲሁም የስታርታፕ ምኅዳሩን ዕድገት ለማስፋፋት የሚያስችል የሙከራ ፈቃድና ክትትል ስርዓት ሊቀርጽና ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ተጨማሪ የብቁነት መስፈርቶችን የማመልከቻ ሒደትንና በሙከራ ፈቃድና ክትትል ስርዓት ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሁኔታዎችን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**37. <u>Regulatory Sandbox</u>**

1/ With the objective of fostering innovation and promoting the growth of the Startup Ecosystem, the Ministry may establish and implement a regulatory sandbox framework that will enable testing and introduction of new and innovative products, services, and processes to the market by Startups.

2/ The Ministry may issue a Directive to determine additional eligibility criteria, application process, and other additional conditions applicable for participation in the regulatory sandbox.

**፴፰. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች</u>**

፩/ የንግድ ፈቃድ ለማግኘት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደቅድመ ሁኔታ በተቀመጠባቸው ሁኔታዎች ስያሜ የተሰጠው ስታርታፕ ስያሜ ባገኘ እስከ አራት ዓመት ድረስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ማሟላት አለበት።

**38. <u>Competency Certificates</u>**

1/ In cases where a certificate of competence is required as a prerequisite to obtain a business license, a Designated Startup shall be allowed to fulfill such certificate of competence within Four years of Designation.

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶችን የሚሰጡ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ስታርታፕ የሚያበረታቱ ተገቢ የብቃት መመዘኛዎችን ማውጣት አለባቸው፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ከሕዝብ ጤናና ከብሔራዊ ደኅንነት ጋር በሚያያዙ ዘርፎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**፴፱. <u>የሥራ ፈቃድ</u>**

፩/ በሥራ ፈቃድ ላይ ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ስታርታፕ ውስጥ ሥራ ለመቀጠር የሚፈልግ የውጪ አገር ዜጋ ለሦስት ዓመታት የሚጸና የሥራ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ስታርታፕ በሠራተኛነት ለመቀላቀል የሚፈልግ የውጪ ዜጋ የስታርታፕ ቪዛ የማግኘት መብት አለው፡፡

**፵. <u>የውጪ ስታርታፕ እና ምህዳር ገንቢ</u>**

፩/ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፱ ሥር የሚገኘው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን በውጭ ስታርታፕና ኢትዮጵያ ውስጥ ስታርታፕን በሚመሠርት ወይም በስታርታፕ ላይ ኢንቨስት በሚያደርግ የውጭ ስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፪/ የውጪ ስታርታፕና የውጪ ስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ በዚህ አዋጅ ውስጥ የቀረቡትን ማትጊያዎች በሙሉ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የውጪ ስታርታፕ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሠረት ከሚቀርበው ግራንት ፕሮግራም ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡

2/ Government agencies which are responsible to issue certificate of competence shall issue an appropriate competency requirement which encourage Startups.

3/ Sub-Article (1) and (2) of this Article shall not be applicable on sectors related to public health and national security.

**39. <u>Work Permit</u>**

1/ Subject to the applicable laws on work permit, a foreign national opting to join a Designated Startup located in Ethiopia, shall be entitled to a work permit valid for Three Year.

2/ A foreign national who wants to join a startup in Ethiopia as an employee is entitled to a startup visa.

**40. <u>Foreign Startups and Ecosystem Builders</u>**

1/ The minimum capital requirement stipulated under Article 9 of the Investment Proclamation No. 1180/2020 shall not apply on Foreign Startups and Foreign Startup Ecosystem Builders who establish or invest on Startups in Ethiopia.

2/ Foreign Startups and Foreign Startup Ecosystem Builders shall be entitled to all the incentives provided under this Proclamation.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, Foreign Startups shall not be entitled to the Grant program provided under Article 24 of this Proclamation.

፬/ የኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ቦርድ የውጪ ስታርታፕና የውጪ የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

**፵፩. <u>ስያሜ ለተሰጠው ስታርታፕ የሚሰጥ ከለላ</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ስታርታፕ ስያሜ የተሰጠበትን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሂደትን ማባዛት ወይም የራሱ በማድረግ የስታርታፕ ስያሜን ለማግኘት ሊያመለክትበት ወይም ራሱን እንደ ስታርታፕ በመቁጠር የንግድ ስራ ሊሰራበት አይችልም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

ሀ) በምርቱ፣ አገልግሎቱ ወይም ሂደቱ ላይ ስያሜ ካልተሰጠበት፤

ለ) የአእምሯዊ ንብረት መብት ማስረጃ ከቀረበ፤

ሐ) ከመደበኛው የኢንዱስትሪ አሠራር በቀጥታ መቅዳትን የማያካትቱ ድንገተኛ የመመሳሰል ግጥምጥሞሽ፤ ወይም

መ) በምርቱ፣ በአገልግሎቱ ወይም በሂደቱ ላይ ጉልህ የሆነ መሻሻል ካለ እና ይህም የስታርታፕን ትርጓሜያዊ መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ።

4/ Details about the registration and licensing of Foreign Startups and Foreign Startup Ecosystem Builders shall be determined by a Directive to be issued by the Ethiopian Investment Board.

**41. <u>Protection for Designated Startups</u>**

1/ No person may replicate, utilize, or appropriate the product, service, or process for which a Startup obtained its Designation, nor may they represent themselves as a Designated Startup or engage in commercial activities based on such replication, without the prior written consent of the Designated Startup and approval from the Ministry.

2/ Notwithstanding Sub- Article (1) of this Article, it shall not apply to the following conditions:

a) When a Designation is not obtained on the processes or products, service;

b) A valid Intellectual property right is provided;

c) Incidental similarities arising from standard industry practices that do not involve direct copying; or

d) There is a significant improvement in the product, service or the Process that satisfies the definitional requirement of a startup.

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፪. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ ሕግ ወይም ልማድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፵፫. ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ያወጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**፵፬. አዋጁ የሚጸናበት ቀን**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## PART SEVEN

## MISCELANEOUS PROVISIONS

**42. Inapplicable Laws**

No law or customary practice, inconsistent with this Proclamation, shall have effect with respect to matters governed by this Proclamation.

**43. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry shall issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**44. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 2nd day of September, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**